# ድልና ተስፋ በአንድነት ኃይሉ መንደር
## ሐፍረትና ውርደት በአፈንጋጩ ሰፈር

ከኃይለ ልዑል ግርማ
ዋሽንግተን ዲሲ

በዚህች አጭር ጽሑፍ በቅንጅት እውነተኛ አመራርና በአፈንጋጩ ቡድን መካካል ያለፉትን ሶስት ወራቶች የፖለቲካ ዝብርቅርቅ ሁኔታዎች በትንሹ ዳሰስ ለማድረግ እሞክራለሁ:: መቼም ሁሉ ተነስቶ ሁሉ ተጽፎ ወይም ተነግሮ አያልቅምና በመጠኑ ጠቀስ፣ ዳሰስ ላድርገው::

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የአፈንጋጩ ቡድን ጉዳይ ፈጻሚዎች ወይም የወያኔ የፖለቲካ ወያላዎች የታዘዙትን ካልሰሩ ጥቅማቸው ይቀርባቸዋልና፣ ቃል የተገባላቸው ሁሉ ይበላሻልና እንደታዘዙት ለማድረግ የማይቧጥጡት ዳገትና መሬት የለም:: በሁሉም አገርና በየትኛውም ቦታ ግን አንድ ተመሳሳይ ባህርይ አላቸው:: ይኸውም መዋሸት፣ ግራ ማጋባትና ሕዝቡን መከፋፈል ናቸው:: የሀሰትና የውሸታቸው መጠን ግዙፍነት እየጨመረ፣ በሬ ወለደ ብቻ ሳይሆን መንታ መንታ ወለደ ልፈሩቸውን እያራቡና እንደ አበደ ውሻ ያንንም ያንንም መለካከፋቸው እየቀጠለ ሲሄድ፣ በዚያው አንጻር ደግሞ ሕዝብ ማንነታቸውን እያወቀ፣ እየራቃቸውና እየተቃወማቸው መጥቷል:: እስቲ ጥቂቶቹን ላንሳቸው::

1ኛ/ የቅንጅቱ ፕሬዚዳንት ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በታመመ ሰውነታቸው በከዘራ እያዘገሙ በምርጫው ሳቢያ ቤተሰቦቻቸው የተገደሉባቸውን ሰዎች ማጽናናታቸውና የገንዘብ እርዳታ ማድረጋቸው ሲታወስ፣ የአፈንጋጮቹ ቡድን ከሞትና ከአሜሪካ የሚቀር የለም ብለው ወደ አሜሪካ ከሮጡ በኋላ የቅንጅቱ ፕሬዚዳንት ያደረጉትን ከዜና ማሰራጫዎች ሲሰሙ የተከፉበትና እስከ ዛሬ የሚከነክናቸው ነገር ነው:: ኸረ ለመሆኑ ለምንድነው የሚች ቤተሰቦች መረዳትን የቅንጅት አመራር ነን የሚሉ ሰዎች የሚቃወሙት? ለምንድነው ለተባለው እርዳታ ገንዘብ ከባንክ ወጪ እንዲሆን ኃላፊ የነበሩና የአፈንጋጩ ቡድን ደጋፊ የሆኑት ግለሰብ በወጪ ቼክ ላይ አልፈርምም ያሉትና ችግር ለመፍጠር የሞከሩት? ዛሬስ ከስንት ወራት በኋላ ነገሩን እነዳዊት ከበደ አንስተው የቅንጅቱ ፕሬዚዳንትን ለሚች ቤተሰቦች መጽናኛ ላደረጉት እርዳታ ከእውነት እርቀው ስማቸውንና ስራቸውን የሚያጎድፉት? የቅንጅት አመራር ሳይንቀሳቀስ በፊት አገር ቤት እያለ ሕዝቡን እንዲያነጋግሩ በፕሬዚዳንቱ እየተነገራቸው አይደለም እንዴ የአሜሪካ ደጋፊዎች ይበል ጡብናል ብለው አብሮ የተሰቃየውን ሕዝብ ሳያጽናኑና ሳያመሰግኑ፣ የቅንጅቱን ሕልውና ጉዳይ ፎር ሳያሲይዙ፣ ቅድሚያ የሚሰጠውን ስራ መስራት ትተው የሮጡት? ይህን ለማድረግ ወደ ሁለት ወር ገደማ ያህል እኮ አገር ቤት ነበሩ ለምን አላደረጉትም ? ዳሩ ግን ዓላማቸው ሌላ ስለነበር ነው ወደ አሜሪካ የሸመጠጡት::

2ኛ/ የአፈንጋጩ ቡድን አሜሪካ ከመጣ በኋላ ጉሮ ወሸባዬ፣ የአበባ ጉንጉኑና ግብዣው በደስታ አስክሮዋቸው እንደ ድል አድራጊ ጭፈራና ሆይ ሆይታው ቀልጦ ሲቀልዱብን የከረሙት:: እነ ብርቱካን በየከተማው እየሄዱ ድራማ መስራት፣ መዘባረቅ፣ ውሸት መዋሸት፣ ወያኔን ለማስደሰት ይቅርታ መጠየቅ፣ በቅንጅት ስም ገንዘብ መሰብሰብ፣ የመከፋፈሉና የማፈንገጡን ሁኔታ ማባባስና የልባቸው ሲደርስ ወደ አገር ቤት ተመለሱ:: በመጀመሪያ ደረጃ የመጡት የራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ይዘው መሆኑን እራሳቸው በተግባር አረጋግጠውልናል:: በኖቬምበር 2005 መጀመሪያ ላይ መሪዎቻችን የታሰሩበት፣ በ10 ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች በዝዋይና ደዴሳ የተወረወሩበትና ለበሽታና ለአውሬ የተጣሉበት እና ብዙዎች በአዲስ አበባ ግንባራቸውን በጥይት እየተመቱ ሕይወታቸውን ያጡበትን ጊዜ በሀዘን በማሰብና የተሰዉትን በማስታወስ ፈንታ እነ ብርቱካን ሚዴቅሳና አቶ ደበበ እሸቱ በዚያው የመታሰቢያ እለት ወደ ካናዳ ሄደው ዳንኪራ ሲረግጡና እስክስታ ሲወርዱ ማምሸታቸውን በቪዲዮ ስንመለከት የስንቶቻችን አንጀት ነው እርር ድብን ያለው:: መሪዎቻችን እንዲፈቱ ብለን የጮኸነውን ያህል እውነት ለእነዚህ ጨካኞችና ከዳተኞች ነወይ ብለን በራሳችን እንድናፍር አድርገውናል:: የአፈንጋጩ ቡድን መሪ ደግሞ አሜሪካ ሥራ አግኝተዋል ተብሎ እንደሚቆዩ ተረጋግጧል:: የሚወራው ነገርማ እውነት ከሆነ እውነትም ሰውዬው "አራዳ" ናቸው:: በአጠቃላይ እነዚህ ጥቂት ግለሰቦች እንደነዚህ አይነት አሳፋሪ ዜናች መሆናቸውን አረጋገጡልን:: ወይ አለማወቅ ወይ መሞኘት::

3ኛ/ የቅንጅት መሪዎች በታሰሩበት ወቅት በየቦታው የነበሩ ቢሮዎች የተዘጉ ቢሆንም በአንዳንድ ቦታዎች የነበሩ የቅንጅት ቢሮዎች በጥቂት ሰዎች ጽኑ እምነትና ትግል የቢሮ ኪራያቸውን እየከፈሉ ቢሮዎቹን ሳያስነጥቁ አቆይተው የቅንጅት መሪዎች ከቃሊቲ ሲወጡ ቢሮዎቹ እንደ ቀድሞ እንዲሰሩ ለማድረግ ኃላፊነታቸውን ሲያስረክቡ፣ ይህንን በማበራታትና በመደገፍ ፈንታ የአፈንጋጩ ቡድን ደጋፊዎች "እነዚህ ቢሮዎች

መከፈት የለባቸውም" ብለው ሽንጣቸውን ገትረው ተሟግተዋል፡፡ ጉድ ነው፡፡ የቅንጅት አመራር ላይ ያለ ሰው የቅንጅት ቢሮ እንዳይከፈት ያደርጋል ብሎ የሚያስብ ማን አለ? አዎን ይህ ተደርጓል፡፡ ለምን ሲባል ቢሮዎቹ የመኢአድ ስለነበሩ መከፈታቸው ትክክል አይደለም ይላሉ፡፡ ድሮስ በመላው ኢትዮጵያ ያሉት የመኢአድ ቢሮዎች አይደሉም እንዴ የቅንጅት ቢሮ የሆኑት? በየክፍለ ሀገሩ ያሉት ቢሮዎች ካልተከፈቱ እኮ ሕዝቡን ማግኘት አይቻልም፡፡ ታዲያ የሚፈለገው ሕዝቡ ጋር ግንኙነት እንዳይደረግ ከሆነ እነዚህ ሰዎች ከዚህ የበለጠ ለወያኔ ማገልገላቸው ሌላ ማስረጃ ያስፈልጋልን? ደግነቱ እነርሱ በአሜሪካ ጥቂት ቢሮዎች በአዲስ አበባ ጥቂት ደጋፊ ካላቸው ለእነርሱ ይበቃል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ስሜቱና ፍላጊቱ የተለየ ነው፡፡ የአፈንጋጩን ቡድን ዓላማ ተረድቶ በሰሜን ይሁን በደቡብ በምዕራብ ይሁን በምሥራቅ ኢትዮጵያ ያሉ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች ለቅንጅቱ ፕሬዚዳንት ሙሉ ድጋፋቸውን በመግለጽና የአፈንጋጩን ቡድን አፍራሽ ስራ በማውገዝ ላይ ይገኛሉ፡፡ ቅንጅት የሕዝብ ፓርቲ ነው የምንለውም ለዚህ ነው፡፡

4ኛ/ እነ ዶክተር ብርሃኑ፣ ወይዘሮ ብርቱካን፣ አቶ ግዛቸውና ሌሎቹ ወደ አሜሪካ ሲመጡ አንደኛው አቸኳኮላቸው የቅንጅቱ ፕሬዜዳንት ሕክምናቸውን ጨርሰው ስራ ሳይጀምሩ እነርሱ ደጋፊዎቻቸውን ይዘው አወናብደውና ሆይ ሆይ ብለው ከውጭው ነዋሪ ላይ በቅንጅት ስም ገንዘበ ሰብስበው መሄድ ነበር፡፡ የተሳካላቸው ነገር ቢኖር አንዱ እርሱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ሕዝብ ይህንን ይጠይቃል፤ አንደኛ የብርሃኑ ነጋ መጽሐፍ የተቸበቸበው ለቅንጅት እርዳታ ይውላል ተብሎ ነው፡፡ ምን ያህል ተሸጠ? ገንዘቡ የት ገባ? መታወቅና ለቅንጅት ገቢ መሆን አለበት፡፡ ሁለተኛ፡ በሁለት ወር ጉብኝታቸው የሰበሰቡትን ከግማሽ ሚሊዮን ያላነሰ ገንዘብ ሁሉ ለቅንጅት ሥራ በቅንጅት አካውንት ማስገባት አለባቸው፡፡ እንዳሰቡት ገንዘቡን ለጥፋት ዓላማቸው እና ደጋፊዎችን ለመግዛት ሊያውሉት አይችሉም፡፡ በዚህም መሰረት በገንዘቡም አለማስረከብና በግለሰብ አካውንት ማስቀመጣቸው በራሱ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚያ ውጭ ደግሞ፤ የወጣቱ ክፍል እንደበፊቱ ወደ ቅንጅት ቢሮ እየመጣና እየተደራጀ፣ የሴቱ ክፍልም እንደዚያው እየተደራጀ ለመሪውና ለፓርቲው ድጋፉንና ፓርቲውን የማዳን ስራው ላይ እየተረባረበ ነው፡፡ በሰሜን አሜሪካ ከ40 እና 45 ዓመት በላይ የሆኑ ጎልማሶች በወጣት ስም ጥቂት ልጆቻቸውን ይዘው "የወጣት ሊግ" ነን ገለመሌ ቢሉ ምን ሊፈይዱ? ከአገር ቤት ያሉ ወጣቶች በስማችን ዳግም መነገድ አይቻልም ብለው ሲያስታውቁ የአሜሪካኖቹ ጎልማሶች ወይም "የወጣት ሊጎች" የለም ጽሑፉ የመጣው ካገር ቤት ሳይሆን ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት ናቸው ከአቶ ታምራት ጋር የጻፉት ሲሉ አብበናል፡፡ መቼም ዶክተር ታዬ ፈርዶባቸው የማይወነጀሉበት ወንጀል የለም፡፡ የነብርሃኑ ነጋ ና ብርሃነ መዋ "ወጣቶች" ወደ አገር ቤት ብቅ በሉና የወጣቱን ስራ ተመልከቱ ከማለት ውጭ ምን ይባላል፡፡

5ኛ/ የአፈንጋጩ ቡድን በየሻይ ቤቱ እና በየግለሰብ ቤቱ ሲዶልት ቆይቶ ለከረንት አፌርስ የፓልቶክ ክፍል በስልክ ከቅንጅት ቢሮ ለማስተላለፍና ቢሮውን ተቆጣጥረናል ለማለት በጨለማ የቅንጅትን ቢሮ በጉልበት አስከፍተው ለመግባት ያደረጉት ሙከራ አልተሳካም፡፡ ብዙዎቻችን ስለዚህ ሁኔታ በጥበቃ ስራ ላይ የነበሩት ሰው በቃለመጠይቅ ላይ የሰጡትን በድምጽ የተቀዳውን ሰምተናል፡፡ በእነርሱ ደረጃ ያለ ሰው እንደዚህ ዓይነት ተራ ሙከራ ያደርጋሉ ብሎ አይታሰብም ነበር፡፡ ራሳቸውን አዋረዱ፡፡ ከዚያም በኋላ ጋዜጣዊ መግለጫ እንሰጣለን ብለው በድፍን አዲስ አበባ የሚከራዩት ቦታ ጠይቀው አጡ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊቱን ስላዞረባቸው የሚደግፋቸው አጡ፡፡ ሕዝብ ስራቸውን ስለሰማ ወጊዱ ነው ያለው፡፡ ሕዝብ ራቃቸው፡፡ ናቃቸው፡፡ ተቃወማቸው፡፡

6ኛ/ ክቡር አንጂነር ኃይሉ ሻውል በታሕሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ለላዕላይ ምክር ቤት የአምስቱን የቅንጅት አመራር አፈንጋጮችን ቡድን በሚመለከት የወሰዱትን እርምጃና ያስተላለፉትን መመሪያ በመቃወም አምስቱ አፈንጋጮች የተቃውሞ መልስ ሰጥተዋል፡፡ አዎን የተጠበቀ ነበር፡፡ ያጠፊቸውን ጥፋቶች ሁሉ በመካድ ጨርሶ "አሉባልታና ሀሰት ነው" ለማለት ሞክረዋል፡፡ ድሮም እኮ አዎን ጥፋቱን የሚያምን መታረም የሚፈልግና በዚያው ጎዳና መቀጠል የማይፈልግ ነው፡፡ አምስቱ አፈንጋጮች ያተረፉት ነገር ቢኖር ትዝብትና በሕዝብ መናቅን ብቻ ነው፡፡ የፓርቲ አመራር ነንና ያፈለግነውን መስራት እንችላለን የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ስላላቸው በዚያው የአፍራሽ ስራቸው ሲቀጥሉ፤ ፕሬዚዳንቱ የድርጅቱን አደጋ ላይ መውደቅ በመገንዘብ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ለላዕላይ ምክር ቤት መመሪያ መስጠታቸው ያልጠ በቁት ነገር ነው፡፡ የሕዝብ ፓርቲ መሪ፣ የሕዝብ አደራ የተቀበለ መሪ ኃላፊነት አለበትና ድርጅቱን ለማዳንና ለመጠበቅ አጥፊዎቹን አያማክርም ወይም አይጠይቅም ትክክለኛውን ውሳኔና እርምጃ ይወስዳል እንጂ፡፡ የክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን እርምጃ በሀገር ቤቱ ሕዝባችን እሰይና እልል ብሎ እንደተቀበለው በትላንቱ እለት ካገር ቤት ያሉ ከፍተኛ አመራሮች ሲገልጹ ሰማን፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእነዚህን አፈንጋጮች ሴራና ጥፋት አውቆ ፊቱን አዙሮባቸዋል፡፡ ነገ ደግሞ ለፍርድ ያቀርባቸዋል፡ ጥርጥር የለውም ምክንያቱም መስዋዕትነት የከፈለበት ትግሉ ነውና፡፡

7ኛ/ በለመዱት የውሸት ፕሮፓጋንዳ ክፍሎቻቸው እንዳዊት ከበደ ከ60 ዎቹ የላዕላይ ምክር ቤት አባሎች 12 የሚሆኑት ብቻ ኢንጂነር ኃይሉን ሲደግፉ 43 ያህሉ ተቃውሚቸዋል ብለው የስም ዝርዝር ለጠፉ። አቤት በገዛ እጅ መዋረድ። አዎን በእነርሱ ቤት ኢንጂነር ኃይሉ ደጋፊ የላቸውም እነ ብርሃኑ ነጋን የሚደግፈው ይበልጣል በማለት ሕዝቡን ግራ ለማጋባት ነበር። እውነቱ ግን ከዚያ የተለየ ነው። የስማቸውን ዝርዝር እዚያ ተቃዋሚ ክፍል ውስጥ የተመለከቱ ብዙ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ቁጣቸውንና ግራሞታቸውን ሲገልጹ ተሰምቷል። ማን እና ለምን ስማቸው ከእነ ብርሃኑ ነጋ አፈንጋጭ ቡድን ጋር እንደደባለቀው የሚያውቁት ነገር የለም። በዚህ ጉዳይ ላይ በቅርቡ ቃለመጠይቅ ተደርጎ የአፈንጋጩ ቡድንን ሴራና ደባ ማጋለጥ ጀምረዋል። አዬ ዳዊት ከበደና ኤልያስ ክፍሌ አይናቸውን በአሞሌ ጨው ማጠብ ለምደዋልና "የእንግሊዝ ጨው" ነው የሚባለው ለሆድ ማዕዳት የሚወሰደው መድኃኒት እርሱን ፈልጉላቸው እስቲ የሚረዳቸው ከሆነ። እውነቱና ሐቁ ግን ከ31 በላይ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት በክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል አመራር ጋር የቆሙና የሚሰሩ ሲሆን የአፈንጋጩ ቡድን ደጋፊዎች ቁጥር ከአምስቱ አፈንጋጮቹ ጋር 14 ብቻ እንደሆነ ታውቂል።

8ኛ/ በዲሴምበር 15 ቀን 2007 ዓ.ም በዲያስፖራ የፓልቶክ የውይይት ክፍል ከኢትዮጵያ ከ10 ባለይ የላዕላይ ምክር ቤት አባሎች፣ ከአሜሪካ የቅንጅት ፕሬዚዳንት ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል፣ 5 የላዕላይ ምክር ቤት አባሎችና የቅንጅት ዓለም አቀፍ ምክር ቤት ሊቀመንበር ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት፣ ከአውሮፓና ከአሜሪካ እንዲሁም ከካናዳ የቅንጅት ድጋፍ አባሎችና አመራሮች እንዲሁም ከ500 በላይ ታዳሚዎች በተገኙበት እጹብ ድንቅ የተሰኘ የውይይትና መድረክ መካሄዱና፣ የታህሣሥ 1 ቀን ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቅንጅት ፕሬዚዳንት የወሰዱትን እርምጃ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ድምጻቸውን ያሰሙ፣ ለፓርቲው እድገትና የወደፊት ስራ አስተያየት የሰጡና ቃል የገቡ፣ ምክርና ጠቃሚ ጥቆማ የሰጡ ሰዎች የአንድነት ኃይሉን ክፍል ተስፋ ሰጥተው፣ አጠናክረውና አንድ እርምጃ ወደፊት እንዲገፉ አድርገውታል። የቅንጅቱ ፕሬዚዳንትም በዚህ የውይይት መድረክ ከኢትዮጵያና በመላው ዓለም ካሉት የስራ ጓዶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ጋር ለመወያየትና ድምጻቸውን ለመስማት በመቻላቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸውና አመስግነው ሁላችንም የምንናገረውን በተግባር እንድናሳይ አሳስበዋል። ድል በአንድነት ኃይሉ ጎራ፤ እፍረት፣ ተስፋ መቁረጥና ጭንቀት በጸረ አንድነቱ ጎራ ሰፍኖ ውሏል። አዎን የማይቀረው ድል የአንድነት ኃይሉ ክፍል ነው። ሰላም ቆዩ። አፈንጋጮችም አፈንግጣችሁ ቅሩ። አትጠቅሙንም የጠላት መሳሪያዎች ናችሁና።

ታህሣሥ 6 ቀን 2000 ዓ.ም
ዋሽንግተን ዲሲ